# ሁሉም እንዲያውቀው
# የአንጃው የቀቢፀ ተስፋ አሳፍሪ ተግባር
## ከታዛቢ

በኢትዮጵያ የዘመናዊ ፖለቲካ ድርጅቶች ታሪክ ውስጥ ከፅንሱ ጀምሮ በውስጥና በውጭ እሳት እየተለበለበ፤ አባላቱ ቃላት ሊገልፁት በማይቻል ታላቅ ኢትዮጵያዊ አርበኝነት በሞት ጥላ ስር በማለፍ ሰማእትነትን እየተቀበሉ እስካለንበት ሰአት ያደረሱት አንድ ድርጅት ቢኖር ታሪካዊው ኢህአፓ ለመሆኑ የሚጠራጠር ያለ አይመስለኝም:: ውጫዊው እሳት አምባ ገነኑ ደርግና ፀረ ኢትዮጵያዊው ወያኔ ሲሆኑ የውስጡ እሳት ደግሞ በየታሪክ መዳረሻ ወቅት ብቅ እያሉ የተገነባውን የሚያፈርሱ ለሁለቱ አምባገነን መንግሥታት በቅጥረኛነት ያደሩት አንጃዎች ናቸው:: በፀረ ደርጉ ትግል ወቅት በከተሞች የኢህአፓን ድርጅታዊ መዋቅር ለመጀመሪያ ጊዜ ለደርግ ምርመራ ክፍል በማጋለጥ ታሪክ ይቅር የማይለውንና ትውልድ የበላውን የቀይ ሽብርን ፍጅት የተባበሩና ያራመዱ፤ የትግል ጓዶቻቸውንና መልምለው ወደድርጅቱ ያመጧቸውን አባላት ሳይቀር በሰይል የዘለዘሉ፤ በፈላ ዘይት የጎነፉ በገጠሩ ትግል ደግሞ የወያኔ የውስጥ ሰላይ በመሆን ድርጅቱ ላይ ታላቅ የብተና ሴራ ካከናወኑ በኋላ ኢህዴን የተባለ ቃጭል ተንጠልጥሎላቸው ለወያኔ በገሀድ ያደሩት የዛሬዎቹ በረከት፤ አዲሱ ታምራትና..... መሰሎቻቸው ይገኙበታል::

የዘመነ ደርጉ የመብት ትግል በዘመነ ወያኔ ሀገርን በማዳን ትግል በመተካቱ ትግሉ እየመረረም እየረዘመም የመቀጠሉ ሀቅ ፅናትንና መርህ የሚገዛው ሰብእናን ጠያቂ፤ ከጊዜያዊ የጥገና “ድል” ዘለቄታዊና ሁሉን አሳታፊ ሥርአት እውን ለማድረግ ለረጅሙ ጉዞ የተዘጋጀና ትግሉን ህይወቱ ያደረገ ታጋይ ግድ ይላል:: ይህ በርግጥም ዝና፤ግላዊ ጥቅምና የሥልጣን ጥም ለሚያማልለው ልክስክስ ሰብእና ክፉ ፈተና ነው:: በመሆኑም ትግሉ በረዘመና ድል በራቀ ቁጥር አቋራጭና ርኩስ አማራጭ ፈላጊው ወደሴራ ፖለቲካ በመውረድ ተደራጅቶ በድርጅቱ ላይ ዘመቻ ይከፍታል:: ያዳከመውን ድርጅት በድካም ከሶ ስለደከምን በመርሆችን እንደራደር ማለት ይጀምራል ጊዜውንም ጠብቆ አንጃ ሆኖ ራሱን ይወልድና ይፈረጥጣል:: ይህ ሁኔታ በኢህአፓ ውስጥ ባለፈው አመት ገደማ ዳግም ተከስቶ ሌላ ዙር የአንጃ ቅሪት ተግተልትሎ ከድርጅቱ በጠፍ ጨረቃ መኮብለሉ ይታወሳል::

ክስተቱ ያልተጠበቀ ወይም ከመሆን የሚያመልጥም አልነበረም:: ክህደት በምንም መልኩ የሚመረጥ ባይሆንም አንጃዎች ድርጅቱን ብሎም የህዝቡን ትግል ከውስጥ እየቦጠቦጡ የወያኔ ሲሳይ ከሚያደርጉት ገለል ማለታቸው ታላቅ እፎይታ ነው:: አንጃኞቹ ድርጅቱን ጥለው ከኮበለሉ በኋላ የተመኙት ሳይሆን ቀርቶ ኢህአፓ ባስደናቂ ሁኔታ ቀዳዳዎቹን ደፋፍኖ ተጠናክሮ ሊወጣ መቻሉን እያንገበገባቸውም ቢሆን ማመን ተገደዋል:: ይህም ሁኔታ ድርጅቱ ውስጥ ያሉትን ብቻ ሳይሆን የድርጅቱን ጉዞ ከቅርብ ርቀት የሚከታተሉና ጥቃቱን የማይሹ ሁሉ ይህ የአንጃ ቡድን ምን ያህል የድርጅቱን እንቅስቃሴ ጠፍሮት እንደነበር ማረጋገጥ ችለዋል::

የዚህ መልእክት አላማ የድርጅቱን ሃሳብ የማይደግፉ አባላት ለምን ተፈጠሩ አይደለም:: የአንጃው ቡድን አባላት የሚያራምዱትን “አፈዳቪት” የተባለውን የወያኔን እንቀላቀል መስመር ከከፍተኛው አመራር አንስቶ እስከታችኛው የድርጅቱ

እርከን ድረስ መላው አባላት ተወያይተው ውሳኔ ያሳለፉበት ሂደት በራሱ ማንኛውም አባል ሃሳቡን የማራመድ ያልተገደበ መብት እንዳለው ገላጭ ነው:: ችግሩ የተፈጠረው የቡድኑ መሰረታዊ አላማ አብዛኛው አባል ለተስማማበት ውሳኔ ራስን አስገዝቶ ትግሉን አንድ እርምጃ ማራመድ ሳይሆን ቡድኑ የሚያራምደው ሃሳብ ተቀባይነት ከሌለው ኢህአፓ መፍረስ አለበት የሚል በመሆኑ ነው::

ቡድኑ ድርጅቱን ጥሎ ከኮበለለ በኋላ ላለፈው አንድ አመት ያህል የተሰማራውም ወያኔን በመታገል ሳይሆን ኢህአፓን በማዳከምና ለማፍረስ በመጣር እንዲሁም ኢትዮጵያዊነትን የካዱና የወያኔን ሥርአት በተለየ መልኩ ለማስቀጠል የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦችና ቡድኖችን አላማ በማስተጋባት ተግባር ላይ ለመሆኑ ባቋቋመው ፓልቶክ ሩሙና በተለያዩ አፍራሽ እርምጃዎቹ አረጋግጦታል:: ይህም ሁኔታ ከራሱ አባላት ሳይቀር ተቃውሞን አስነስቶበታል:: ቡድኑ ካደረሳቸው ጥፋቶቹና ወንጀሎቹ መካከል የኢህአፓን ስምና የልሳኑን መጠሪያ በመዝረፍ ለአፍራሽ አላማው ማራመጃ ማድረጉ ሲሆን ይህ ደግሞ ከቀደሙት አንጃ ቡድኖች ሁሉ የከፋ ያደርገዋል::

ድርጅቱ እኔ ነኝ ያለእኔ ፀሐይም አትወጣለትም የሚል ሰባኪ ተከትለው “ታሪክ” ሊሰሩ ከኢህአፓ ኮንግረስ በጠፍ ጨረቃ የኮበለሉት የአንጃ አባላት ያሰቡትና የተዋሸላቸው ሁሉ ሀሰት መሆኑን ሳይውል ሳያድር ሲረዱት፤ ይጠፋል ያሉትም ኢህአፓ ማንም ሊክደው በማይችል ሁኔታ ባይናቸው ፊት እየጠነከረ መምጣቱን ሲገነዘቡት ሀፍረት፤ ብስጭትና ተስፋ መቁረጥ የወለደው አስነዋሪ ባህርይና አልፎ ተርፎም በህግ ሊያስጠይቅ የሚችል ተራ የወሮበላ ወንጀል ውስጥ እየተሰማሩ ይገኛሉ::

የአንጃው አብዛኛው አባላት በሚገኙበት በቶሮንቶ ካናዳ የሚገኙት ግለሰቦች ዋነኛ ተግባር የኢህአፓን የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ለማደናቀፍ ከሚጥሩባቸው ስልቶች አንዱ ግለሰቦች ትግሉን እንዳያግዙ በተለያየ ምክንያት ለሚያውቋቸውና ለሚያገኙዋቸው ወገኖቻችን ፓርቲው ውስጥ ስለፈጠሩት የብተና ሙከራ የተዛባ መረጃ ማቅረብ፡ድርጅቱ ህዝባዊ ስብሰባ ሲጠራ ይህንኑ ለማደናቀፍ ውዥንብር መንዛት፤ ስብሰባም ሲካሄድ በቡድን ሆኖ ከስብሰባው አጀንዳ መንፈስ ውጭ ለመበጥበጥ መሞከር፤ የጥሪ ማስታወቂያዎችን ቀዶ መጣል፤ ተመሳሳይ ስብሰባ በተመሳሳይ ጊዜ መጥራትና እንዲሁም ተራ ዘለፋ ስም ማጥፋትና ስድብ  ከአስነዋሪ ተግባራቸው መካከል የሚጠቀሱ ናቸው:: ይህን መሰሉ ሁኔታ ከዚህ ቀደም በተደረጉት ልዩ ልዩ ስብሰባዎች የተከሰተ መሆኑ የተጠቀሰ ነው፤ ለምሳሌ አንጃው ገና ሳይፈረጥጥ በአመሪካ (ዳላስ ቴክሳስ) ውስጥ በተደረገ የቀድሞ የፓርቲው (የኢህአፓ) አባላት ማሰባሰብ ስብሰባ ላይ ከተራ ስድብና ዘለፋ በላይ ጸንተው በትግል ላይ ያሉ አባላትን ለመደብደብ መገልገላቸው ይታወቃል:: ይህንን አሳፋሪ ባህሪም የድርጅቱ አባል ያልሆኑ በተለያዩ መድረኮችና ድርጅቱ በጠራው ስብሰባ ላይ የሚገኙ ወገኖች የአንጃው ቡድን አባላት ከእንዲህ አይነት ጤናማ ያልሆነ ተግባር እንዲቆጠቡና ይልቁንም ይቅርታ ጠይቀው ወደድርጅቱ ቢመለሱ የተሻለ እንደሚሆን ምክር የተቀላቀለበት አስተያየት ትዝብትና ሀዘናቸውን ገልፀውላቸዋል::

በቅርቡም የአንጃው ቡድን አንድ አባል የግለሰብ ነፃነትንና መብትን በእጅጉ በሚጋፋ ሁኔታ በወያኔ የታሰሩ እስረኞችን ለማስፈታት በቶሮንቶ ከተማ የተቋቋመውን "የተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን በቶሮንቶ" የተባለው ኮሚቴ የጠራውን የህዝባዊ ስብሰባ ጥሪ ማስታወቂያ ሲያሰራጭ የነበረውን አባል ብቻውን አገኘሁት በሚል የድብደባ ሙከራ አድርጓል:: ጥቃቱ የተሰነዘረበት ወገናችን "ጥፋቱ" የዛሬዎቹ አንጃዎች ትላንት እንታገልለታለን ይሉት የነበረውን ህዝባዊ አላማ በፅናት መቀጠሉ ብቻ ነው:: ይህ ሁኔታ የሚያስገነዝበን ጥቃቱን ፈፃሚው ግለሰብ በአካል በሀያአንደኛው ክፍለ ዘመን ቶሮንቶ ከተማ ቢገኝም በተግባሩ፤ በባህርዩና ባስተሳሰቡ ግን የመካከለኛው ዘመን ወሮበላ መሆኑን ነው::

የሚገርመው እነዚህ ግለሰቦች ህግ ባለበት አገር ይህን ያህል በእጅጉ ሊያስጠይቅ የሚችል ወንጀል ከመፈፀም ካልተመለሱ ለመለስ ዜናዊ ያቀረቡት የፈርመን እንግባ ማመልከቻ ተቀባይነት ካገኘ ህግ በሌለባት ኢትዮጵያ ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ መገመት አያዳግትም:: ከዚያ መሰሉ የመቀርጠጥና የማስበላት የፍጅት አዙሪት ይሰውረን:: ራሱን "ዴሞክራቲክ" እያለ የሚያመፃድቀው ቡድን እንዲህ ባጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ተራ ወሮበላነትና የጠረባ ቡድንነት መሸጋገሩ በራሱ ቡድኑ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ገላጭ ነው::

የህዝብ ወገኖችን ማሳደድ ወያኔያዊ ወንጀል ነው!
ፀረ ወያኔው የነፃነት ትግል ይቀጥላል!